# <u>አዲሱ ዘመቻ! ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ ወደ መለስ ዜናዊ እየተቀየረ ነው</u>

(ከዳዊት አበሩ - ሜልቦርን)

ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ሁላችንም እንደምናየው እንደ ኢትዮ-ሚዲያ ባሉ ነፃ የ ኢንተርኔት ዜና እና አስተያየቶች ማዕከላት ወይም በሌሎች የወሬ ምንጮች (የዘረኛው መንግሥት የራሱን እና በግልፅ ወይም ስውር በሆነ መንገድ ለመርዘኛ ፍልስፍናው አፈ-ቀላጤ የሆኑ የኢንተርኔት ‘ዌብ ሳይቶች’ን ጨምሮ)  እየተነገረ ባለው ዘመነኛ ወሬ፣ መከራዋ ማለቂያ ያጣ በሚመስለው አገራችን አንድ አዲስ፣  እንግዳ-መሰል ግን ያልተጠበቀ ያልነበረ ዜና እየተነገረ ነው። ሁላችሁም ሰምታችሁ ሲሆን እንደሚችለው አዲስ - ግን በዘረኛው መንግሥት በጥንቃቄ የተቀመረ “ መለስ ዜናዊ ከመድረኩ ከተገለለ አገሪቷ ድምጥማጧ መጥፋቱ ነውና ሰውዬው ከሚቀጥለው ‘ምርጫ’ በኋላም ሥልጣኑን ይዞ እንዲቀጥል እንማፀነው” የሚል ዓይኑን ያፈጠጠ ዘመቻ ተጀምሯል!

ብዙዎቻችን እንደሰማነው መለስ ዜናዊ በቅርብ ወራት ከ ዓለም-አቀፍ የዜና ወኪሎች ጋር በሚያደርገው ቃለ-መጠይቅ (Newsweek, Time, The Economist ወዘተ…) በሚቀጥለው ‘ምርጫ’ ስለመወዳደሩ ሲጠየቅ በተለመደው የጮሌ ብልጣብልጥ መልሱ ‘እቆያለሁ’ ወይም ‘አልቆይም’ የሚል ግልፅ መልስ ሳይሰጥ አጠቃላይ የሆነና ግራ የሚያጋባ ግን ‘ሊቀጥል እንደሚገደድ’ የሚያመላክት የሚመስል መልስ መስጠት ጀምሯል።

ሁላችንም እንደምናውቀውም ላለፉት አሥር ዓመታት በማያሻማ መንገድ ለዘረኛው መንግሥት የሥልጣን ማራዘሚያ justification ለኛ ለኢትዮጵያዊያን (የ ኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎችን ጨምሮ) ብቻ ሳይሆን በተለይ እና ምናልባት በበለጠም መንገድ ለደጋፊዎቹ የአውሮፓና የአሜሪካ መንግሥታት የሚሰጠው የሚያስፈራና አማራጭ የሌለው የሚመስል ምክኒያት፡ “ኢሕአዴግ ከሌለ ኢትዮጵያ እንደገና እንዳትድን ሆና ትበታተናለች” የሚለው ‘ሟርት’ ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዘረኞቹ መንደር የተያዘው አዲስ ዳንኪራ ግን መሠረተ-ሃሳቡ እንዳለ ሆኖ “ኢሕአዴግ” የሚለውን ቃል በ “መለስ ዜናዊ” የመተካት ብልጣብልጥ ግን ዓይን ያፈጠጠ ድፍረት ነው። ብዙዎቻችን እንደምስታውሰው ይህ አይነት ልብ-አቅልጥ ድርቅና በቀድሞዋ ሶቪየት ኅብረት፣ በምስራቅ አውሮፓ፣ በቻይና፣ በቬትናም፣ በሰሜን ኮሪያ፣ በካምቦዲያና በኩባ እንደ ሕገመንግሥት ሲማልበት የነበረ የ እብድ ፍልስፍና ነው።

እንደዛም ሆኖ ግን ይሄ የ እብዶች ፍልስፍና በነዛ ሁሉ አገራት ለተበደለው ጎልቶ-መሣፍርት ለሌለው ተራ ሕዝብ አልሠራም እንጂ ለፓርቲው አባላትና ጥቅም ተጋሪዎች ግን ፍልስፍና ብቻ ሳይሆን ሃይማኖት ሁሉ ሆኖ ነበር። በዚህ ምክኒያትም ነው እንደ ስታሊን ዓይነት ምጎረተቢስ የመንደር ዱርዬ፣ እንደ ቻውቼስኮ ያለ የምድር ቀውስ፣ እንደ ሆኔከር ያለ አንጉለ ቢስ የጕረቤት በግ፣ እንደ ቴዎር ዢቭኮቭ ያለ የወፐቤት አንጕል፣ እንደ ፖል ፖት ያለ የዲያቢሎስ መንታ፣ እንደ ኪም ኢል ሱንግ ያለ ምድራዊ 'አምላክ' እንደ ካስትሮ ያለ 'መልዓክ' እና እንደነሱ ዓይነት ጭራቆች በነዛ ሁሉ ከ 1.5 ቢሊዮን በላይ በሆኑ ምስኪን ሕዝቦች ጫንቃ ላይ ለዓመታት ያለጠያቂ ሲጋልቡ የኖሩት።

ስለነዚህ አምባገነኖች ስንነጋገር ከምሥራቅ አውሮፓ አገሮች አምባገነኖች ሁሉ የመጨረሻው ጨካኝና አለምንም ተቀናቃኝ ሥልጣን ላይ ለ 45 ዓመታት በመዘፍዘፍ ድሃ ህዝቡ ትከሻ ላይ የጋለበውን የአልባኒያውን ኤንቨር ሆዣን መጥቀስ በተለይ ለኛ ጉዳይ በቀጥታ የሚገባ (relevant) እና ፊትለፊት ተያያዥ ይመስለኛል። (ለምን እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን)።

ከላይ ስለዘረዘርናቸው አምባገነኖች ያጋጠማችሁን ሁሉ ታሪክ ብታነቡ፣ አሁን እኛ አገር እየሆነ ካለው ነገር ጋር በሚያስደነግጥ ዓይነት የሚመሳሰል ነገር ታገኛላችሁ። ከብዙ በጥቂቱ ስመናገር፣ ለሁሉም የወሰን-አልባ ሥልጣናቸው መሠረት 'ጓድ እከሌ ከሌለ አገሪቷ አትኖርም' የሚለው የወፈፌ መፈክር ነው። "ጓድ ስታሊን ከሌሉ ሶቪየት ኅብረት ትፈራርሳለች!"፤ "ሩማኒያ ያለችው ለጓድ ቻውቼስኮ እና ለጓድ ኤሌና (ሚስቱ ነበረች) ነው! ፤ "አለ ጓድ ኪም ኢል ሱንግና ውድ ልጃቸው አመራር ኮሪያ እንደዳመና ትበናለች!"፤ "ጓድ ፖልፖት (Brother Number One ተብሎ ነበር የሚጠራው በነገራችን ላይ) የካምፑቺያ ህይወት ናቸው!"፤ "ኩባ የምትኖረው ለጓድ ካስትሮ ነው!"፤ እና ከሁሉም የሚገርመኝ ይኼኛው ነው - "አልቤኒያ ጓድ ሆዣ ናት!" አምባገነኖች እንዲህ ሲያብዱና የሚያቆማቸው ሲጠፋ አገር አገር መሆኗ ይቀርና ገለሰብ ሁሉ ትሆናለች።

የሚያሳዝነውና ምናልባትም የሚያስፈራው ነገር እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ሰዎች ሁሉ ከነወሰን አልባ ጥፋታቸው እና ጭካኔያቸው ጋር በየአገራቸው ቢያንስ ሃያ ዓመት ሥልጣን ላይ ተፈናጠው መቆየት እንደቻሉ ሲታሰብ ነው። ያደረሱትን ለመግለጽ የሚያስቸግር በደል፣ ጭካኔ፣ ጥፋት እና መከራ ለማየት ግን ኮሙኒዝም እንደ ጎሞራ ወደውስጥ ፈንድቶ እስኪሞትና ዕልፍ አዕላፍ ህዝቦች ነፃ እስኪወጡ መጠበቅ ግድ ነበር።

የሚገርመው ነገር ብዙዎቹ እነዚህ አምባገነኖች የነሱ በደል ሳይበቃ ሚስቶቻቸውን ወይም ልጆቻቸውን ስነሱ ዓይነት አምባገነን ሥልጣን ሲያሠለጥኑና ሲገሩ መክረማቸውና፣ እሱ ሳይበቃ አቀንቃኞቻቸው ደሞ ከነሱ አልፎ ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ለማምለክና ለማስመለክ እንዴት እንደደከሙና እንደጣሩ ሲታይ ነው። እነዚህ የክፍለ ዘመናችን አምሳያ አልባ መርዘኞች ከሞቱ በኋላ እንኳን ጥላቸው በየዘመዳቸው እንዲቀጥል ምን እንዳደረጉ ዓይተናል። ለ ኪም ኢል ሱንግ - ልጁኪም ጆንግ ኢል ነው፤ ለ ኤንቨር ሆዣ ሚስቱ ኔዚሚዬ ናት፤ ለ ቻውቼስኩ ሚስቱ ኤሌና ናት፤ ለካስትሮ ወንድሙ ራውል ነው...ሌሎችም... ሌሎችም።

በነዚህ ሁሉ አገሮች የዓመታት የጭካኔ፣ የአምባገነንነት እና የጥፋት ትዕይንት መሃል እኔን ሁልጊዜ የሚያስገርሙኝና ለመረዳት የሚያስቸግሩኝ፣ ሰዎቹ (ዋናዎቹ) ሳይሆኑ አጋፋሪዎቻቸው ናቸው። ሳይሞቱ እንደ አምላክ ይሰግዱላቸዋል፣ ሲሞቱ ደሞ በሚስቶቻቸው፣ በወንድሞቻቸው፣ ወይ በልጆቻቸው፣ ማምለክ ይጀምራሉ። እነዚህ አጋፋሪዎች ቀላጤነታቸው ያገጠጠ ሲመስላቸው የፓርቲያቸውና የድርጅታቸው ማሽነሪ ከተራው ሕዝብ መሃል "እከሌ ከሌለማ እንዴት አድርጋ ነው አገር የምትኖረው?!" የሚሉ ህዝብ የሚያውቃቸው ግን ለህዝብ ምንም ያልሆኑ ቀላጤዎችን ማደንና ማዘፈን ይጀምራሉ።

ይኼን ሁሉ አስቡና አሁን እኛ አገር እየሆነ ያለውን ተመልከቱ።

የውጪ ጋዜጣ መለስ ዜናዊን ይጠይቃል...

"After having been in power for so long, will you still run in the next election?"

እና መለስ ይመልሳል...

"I think this will be my last term... but the decision is up to my party, not me."

ከዛ ትንሽ ቆይቶ በረከት የሚባለው የመለስ ዜናዊ "አጋፋሪ-ፊታውራሪ" አገር ውስጥ በሚታተም አንድ እንግሊዝኛ ጋዜጣ ቃለ-መጠይቅ ይሰጣል።

“Do you think Meles Zenawi should run for a third term next election?”

እና ፊታውራሪ በረከት ምን ይሳል?

“Why not?!!”

ከዛ አንድ ሁለት ሣምንት ይቆይና ያው ጋዜጣ ሌላ ቃለ-መጠይቅ ያወጣል።

አሸብር የሚባሉ ለፓርላማ በግል የተወዳደሩ ሰውዬ ናቸው (በኋላ ስሰማ የሆነ እግር ኳስ ምናምን ነገር ሳይ ባለሥልጣን ነበሩ መሰለኝ)

“ስለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምን ይላሉ?”

“እሳቸው ከሌሉማ ምን አገር ተረፈ?! እንደኔ እንደኔ ከሚቀጥለው ምርጫም በኋላ እሳቸው ሥልጣኑን ይዘው እንዲቀጥሉ ኢሕአዴግ መስመን አለበት!”

አስቡ እንግዲህ! እኚህ ሰውዬ የ ኢሃዴግ አባል አይደሉም (ቢሆኑም እኛ አናውቅም)፤ በግል ለፓርላማ የተወዳደሩ ሰውዬ ናቸው፤ሕዝብ ያውቃቸዋል....

የ እስካሁኑ አልበቃምና፣ እባካችሁ መለስን አስደግድገህ ግዛን፣ አጥፋን፣ አቃቅረን፣ አጣላን፣ አለያየን...ብሔራዊ ስሜታችንን ግደልልን...ስለዚህ በሚቀጥለው ምርጫ ራሴን አገላለሁ አትበል ብላችሁ ለምኑልን፤ ኢትዮጵያ የምትኖረው እሱ መሪ ከሆነ ብቻ ነው ይላሉ!

የመለስ ዋና አጋፋሪ ፊታውራሪ ደሞ በየመድረኩ እየተጎማለለ “Why not!!?” ይላል።

ጉዳዩ ይህንን መልክ ሲይዝ በዘረኞቹ ሸንጎ የሚሰማው መፈክር እንደድሮው “ኢሕአዴግ ከሌለ ኢትዮጵያ ትበታተናለች” መሆኑ ቀረና በድንገት ግን በጥንቃቄ በተቀመረ መንገድ “መለስ ከሌለ ኢትዮጵያ ትበታተናለች” ሆኖ ቁጭ አለ! ተዓምር አይደለም!?

እነ መለስ አዲስ አበባ የገቡ ሰሞን ኦነግ የሽግግር መንግሥቱ አባል ሆኖ እያለ አንድ ኢብራሂም መልካ የሚባል የ ኦነግ ሥራ አስፈፃሚ አባል ስለ ብሄር እና አገራዊነት ለመነጋገር ተጠርቶ በነበረ ቃለ-መጠይቅ ሳይ ያለው ነገር ሁሌ ትዝ ይለኛል። በብሔር መከፋፈል የኢትዮጵያን አንድነት አደጋ ሳይ አይጥልም ወይ ተብሎ ሲጠየቅ የሰጠው መልስ፤

“ኦሮሞነቴን ያሳረጋገጠች ኢትዮጵያ ሺህ ቦታ ትበጣጠስ!” የሚል እብሪት ነበር።

እና…

እስካሁን የተነጋገርናቸውን ነገሮች፣ የመለስን ባህርይና የበቀል ተልዕኮ፣ ያጋፋሪዎቹን ድፍረት፣ ያዳማቂዎቹን ግዴለሽነት (ወይስ አድርባይነት ነው?)፣ የኛን ዝምተኝነትና የዘረኞቹን አምባ ፍልስፍና ዓይቼ፣

አዲሱ መፈክራቸው - “መለስ ዜናዊ የማይመራት ኢትዮጵያ ሺህ ቦታ ትበጣጠስ!” ነው ብል ከምንም ሴሳ ነገር ተነስቼ ሲሆን ይችላል?

አሁን በግልፅ በሚያሳዩት አካሄድ የዛሬ 15 ዓመት ደሞ የመለስ ዜናዊ ልጅ 30 ዓመት ሲሞላው “መለስ The Great Leader! ሠናይ (የልጁ ሥም ነው አሉ) The Dear Leader! ቢሉ ወይም የዛሬ ዓመት ተነስተው‘ከቻድ አዜብ (ሚስቱ ናት) በሳል አመራር ጋር ወደፊት!’ የሚል መፈክር ማቀንቀን ቢጀምሩ ይገርማችኋል?

እያቀነቀኑት እንዳለው አዲስ አካሄድ ይሄ አይሆንም ብሎ መጠራጠር ሞኝነት ነው። ነገሩ አንድ ሆኖ፣ ልዩነቱ ምናልባት ‘ማነው ኢትዮጵያዊው?’ የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ይሆን ይሆናል።

ኮሪያን እንኳን ብንመለከት፣ ኪም ኢል ሱንግም ከነ ወሰን-አልባ በደሉ፣ ልጁ ኪም ጆን ኢልም ካባቱ ከወረሰው ክፋት - ምንም ሕዝባቸው ላይ ቢጨክኑ ሁለቱም በማያከራክር መንገድ ኮሪያውያን ናቸው። ምንም ሕዝባቸው ላይ ወደር የሌለው በደል ቢያደርሱ ኮሪያዊነታቸውን ማንም አይጠራጠርም፣ እነሱም አይክዱትም። ብሔራዊ ማንነታቸው ከጥያቄ በላይ ነው። ለድርድርም አይቀርብም።

የኛ ጉዳይ ፈፅሞ እንቆቅልሽ የሚሆነው ታዲያ ይሄ ሲታሰብ ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ የሚመራውን አገር ብሔራዊ ማንነት በግልፅና ባደባባይ የሚያበሻቅጥና የዛኑ አገር አገራዊ ስሜት ያለ እረፍት የሚያቆሽሽ መሪ የተፈጠረባት አገር ምናልባት በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በመለስ መሰሪ ሤራ እየተገዘገዘች ያለችው ያሁኗ ኢትዮጵያ ብቻ ናት።

ሰውዬው የኢትዮጵያ መሪ ሆኖም “ኢትዮጵያዊነት” እንደኮሶ ያንገሸግሸዋል፣ አጋፋሪዎቹ ‘እሱ ከሌለ ኢትዮጵያ አለቀላት!’ እያሉ የንቀት ማርት ያሟርታሉ። እንዲህ ዓይነት የአብደት ንቀት አይታችሁ ታውቃላችሁ? በሁላችንም የጋራ ማንነት፣ በኢትዮጵያዊ ደግነታችንና በበጐነታችን ላይ እንዲህ እንደተሣለቁ እንዲቀጥሉ በቃ ዝም እንበላቸው?

የጋራ አገራችንን ለማዳን ያቅማችንን ሁሉ ከማድረግ እንዳንቦዝን ቃል እንግባ። እግዚአብሔር በቃችሁ ብሎና ምኅረቱን አውርዶ ኢትዮጵያን ይታደጋት ዘንድም እንፀልይ!  እንደመለስ ዜናዊ አጋፋሪዎች መሃላ ሳይሆን እንደ ዕውነቱ ኢትዮጵያን 17 ዓመታት ሙሉ ያስነከሳት እና ውስጧን እንደክፉ ምስጥ እየቦረቦረ ብሔራዊ ስሜቷን የሚያኮላሽ ያገር ጥፋት አርበኛ ካልመራት አገሪቷ ትጠፋለች ብሎ መፎከርና ማስፎከር ህዝብ ላይ መሣለቅ ብቻ ሳይሆን አገር የሚገዘገዝ ብሔራዊ ወንጀል ነው። ብሔራዊ ወንጀል ደሞ  ምኅረት የሌለው ወንጀል ነው። ያ የፍርድ ቀን አይመጣም አትበሉ።

ዳዊት አበሩ

ሜልቦርን

(dawit_aberru@yahoo.com.au)